

# ጎን ለጎን

ደራሲ ጃኔት ጆርጅ

## የመጽሐፍ ቅዱሳዊ እኩልነት አጭር ማብራሪያ

# ጎን ለጎን

ደራሲ  ጃኔት ጆርጅ
ተርጓሚ  ከበደ በከሬ

የመጽሐፍ ቅዱሳዊ  እኩልነት  አጭር  ማብራሪያ

ክርስቲያኖች ለመጽሐፍ ቅዱሳዊ እኩልነት
www.cbeinternational.org

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ያሉት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች የተወሰዱት ከአዲሱ መደበኛ ትርጉም በኢንተርናሽናል መጽሐፍ ቅዱስ ማሕበር በ1993 ዓመተ ምሕረት ከታተመው ነው። መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው።

ጎን ለጎን፣ የመጽሐፍ ቅዱሳዊ እኩልነት አጭር ማብራሪያ
የደራሲው መብት(ኮፒ ራይት) ጃኔት ጆርጅ © 2015 እአአ

**ትርጉም በከበደ በከሬ**

**አሳታሚው**
CHRISTIANS FOR BIBLICAL EQUALITY
122 W Franklin Ave, Suite 218
Minneapolis, MN 55404-2451
www.cbeinternational.org
በመጀመሪያው በአሜሪካን ሀገር ጎን ለጎን፣ የመጽሐፍ ቅዱሳዊ እኩልነት አጭር ማብራሪያ በሚል ታተመ።
ኮፒ ራይት ጃኔት ጆርጅ © 2009 እአአ

ISBN 978-1-939971-27-2 (Print)
ISBN 978-1-939971-28-9 (PDF)
ISBN 978-1-939971-29-6 (ePUB)
ISBN 978-1-939971-30-2 (MOBI)
በዩናይትድ ስቴስ ኦፍ አሜሪካ ታተመ።
መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው። ይህን መጽሐፍ በከፊልም ሆነ በሙሉ ያለአሳታሚው የጽሑፍ ፈቃድ በስተቀር ማንም በማንኛውም መንገድ ማባዛት፣ ማስተላለፍና ማሰራጨት የተከለከለ ነው።

# ማውጫ


**መግቢያ**........................................................................ 1

**በመጀመሪያ**

ፍጥረት........................................................................ 3

ውድቀት........................................................................ 5

**መጽሐፍ ቅዱሳዊ እኩልነት**

በክርስቶስ አንድ ነን.................................................... 6

ኢየሱስና ሴቶች.......................................................... 10

መንፈሳዊ ስጦታዎች.................................................... 13

ሴቶች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ....................................... 15

**በቀድሚ ቤተክርስቲያን የነበሩ አስቸጋሪ ሁኔታዎች**

ዝምታ........................................................................ 16

ሥልጣንና ማስተማር.................................................... 18

ራስነት........................................................................ 21

መገዛት........................................................................ 25

መደምደሚያ................................................................ 26

ስለ ክርስቲያኖች ለመጽሐፍ ቅዱስ እኩልነት (ሲቢኢ)........ 28

ዋቢ መጻሕፍት........................................................ 30

# መግቢያ

በኮሌጅ ውስጥ ለኮሌጅ ተማሪዎች በሳምንቱ መጨረሻ ቀናት በዐውደ ጥናት ላይ እንዳስተምራቸው ተጠየቁኝ። ለፍቅር ጓደኛዬ ይህን ስነግረው ሴቶች ወንዶችን እንዲያስተምሩ መጽሐፍ ቅዱስ አይናገርም ብሎ ሐሳቤን አጣጣለው፡ ፡ ከዚህም የተነሣ ጥያቄውን ሳልቀበል ቀረሁ። ሁለታችንም በተረዳነው መጠን ለመጽሐፍ ቅዱስ መታዘዝ እንፈልግ ነበር። ሆኖም ዐውደ ጥናቱን ተካፈልኩኝ፡ ፡ እኔን በመተካት ያስተማረው ሰው አስደናቂ ሰው ቢሆንም ስኬታማ መምህር አልነበረም። እዚያ ቁጭ ብዬ “ይህ ግን ትክክል አይደለም” እያልኩኝ አስብ ነበር፡ ፡ ከዚያ ከፍቅረኛዬ ጋር የሆነውን ማወቅ ትፈልጋላችሁን? እርሱን አገባሁት! የሚቀጥለው ታሪክ ይህን ይመስላል:

ማትና እኔ በ1978 (እአአ) ጋብቻችንን ጀመርን፤ በዚያን ጊዜ መጽሐፍ ቅዱስ በቤትና በቤተክርስቲያን የአስተዳደር የደረጃ ልዩነት እንዳለ እንደሚያስተምር እናስብ ነበር። ይህ ማለት ወንዶች መሪዎችና ውሳኔ ሰጪዎች ናቸው ማለት ነው። እግዚአብሔር ከሴቶች ይልቅ ለወንዶች ዋጋ ይሰጣል ማለታችን ሳይሆን እያንዳንዳቸው የተለየ ሚና አላቸው ማለታችን ነበር። በጊዜ ሂደት ውስጥ መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምራል ብለን በምናስበውና በእኛ የሕይወት ልምምድ መካከል የማይጣጣም ነገር መኖሩን ተገነዘብን።

ከዚያን ጊዜ ጀምረን በጉዳዩ ላይ በርካታ ሙያዊ የሆኑ ጸሐፎች የተለየ እይታ እንዳላቸው ማየት ቻልን። በእኩልነት የሚያምኑ ወገኖች መጽሐፍ ቅዱስ አማኞች ሁሉ እኩል መሆናቸውን፣ እግዚአብሔር የሰጣቸውን ስጦታዎች በቤት፣ በቤተክርስቲያንና በኅብረተሰቡ ውስጥ ለመተግበር ነፃነት እንዳላቸው ያምናሉ። ይህ ማለት የአገልግሎት ቦታዎች በጾታ ሳይሆን በስጦታና በችሎታ መሰጠት አለበት ማለት ነው። ቤት ደግሞ ባልና ሚስት ለእርስ በርስ በመገዛት፣ በመደጋገፍና አብሮ በመምራት የሚኖሩበት ሥፍራ መሆን አለበት የሚል እይታ ነው።

ነገር ግን ወንዶችና ሴቶች የበላይና የበታች በሚለው ውስን እይታ ምክንያት የሚቸገሩበትን ሁኔታዎች ለመታዘብ ችለናል። አንድ ቀን ወደ ክርስቲያን የመጽሐፍት መደብር ሄድኩኝ። በሴቶች ክፍል ላይ የተቀመጡ መጻሕፍት ስለቶከሌት፣ የሰውነት እንቅስቃሴና ውበት የሚናገሩ ነበሩ። የወንድ ክፍል ደግሞ በመሪነት፣ ገንዘብና ወቅታዊ ሁኔታዎች ላይ የተጻፉ መጻሕፍት ተደርድረው አየሁ። ይህ ለወንድና ሴት ልጆቻችን ምን ዐይነት መልዕክት ያስተላልፋል? ማት እና እኔ ሠርጋችንን የፈጸምንበት ሥፍራ መገዛት ማለት ሚስት ባሏ ስህተት እንኳን ቢሆን እርሱ ያላትን ሁሉ ማድረግ እንዳለባት በሚታሰብበት ቦታ ነበር፡ ፡ የሚስዮን አገልግሎት ላይ የነበሩ ባልና ሚስት ሁለቱም በማስተማራቸው ምክንያት የገንዘብ ድጋፍ እንደተቋረጠባቸው እናውቃለን።

# ይህን ታውቃለችሁን...?

- ጳውሎስ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ “የቤት ራስ” የሚለውን ቃል እንዳልተጠቀመ
- ቅዱሳት መጻሕፍት ሴቶች ለወንዶች ብቻ ሳይሆን አንዳችን ለአንዳችን እንድንገዛ ይናገራል
- በዘፍጥረት ውስጥ ሴትን ለመግለጽ “ረዳት” የተባለው ቃል እግዚአብሔርንም ለመግለጽ በሥራ ላይ ውሏል

እውነትን እንፈልግ፤ ከዚያም ሁላችንም በነጻነት ጎን ለጎን ሆነን ጌታ ኢየሱስን ማገልገል እንችላለን!

# ፍጥረት

እግዚአብሔር “ሰውን በመልካችን፣ በአምሳላችን እንሥራ፣ በባሕር ዓሦች፣ በሰማይ ወፎች፣ በከብቶች፣ በምድር ሁሉ ላይ፣ እንዲሁም በምድር በሚሳቡ ፍጡራን ሁሉ ላይ ሥልጣን ይኑራቸው” አለ። ስለዚህ እግዚአብሔር ሰውን በራሱ መልክ ፈጠረ፤ በእግዚአብሔር መልክ ፈጠረው፤ ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው። እግዚአብሔርም “ብዙ ተባዙ፤ ምድርንም ሙሏት፤ ግዟትም፤ የባሕር ዓሦች፣ የሰማይ ወፎች፣ እንዲሁም በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትን ሕያዋን ፍጡራንን ሁሉ ግዟቸው” ብሎ ባረካቸው (ዘፍጥረት 1፡26-28)።

በዚህ ክፍል ሁለት የሥልጣን መዋቅሮችን እንመለከታን፡ እግዚአብሔር በፍጥረት ሁሉ ላይ ያለውን ሥልጣን እና የወንድና ሴት በአንድነት በመሬትና በፍጥረታት ላይ ያላቸው ሥልጣን ናቸው። ከመጀመሪያውም ወንዶችን በሴቶች ላይ ሥልጣን እንዲኖራቸው ምንም ዓላማ አልነበረም። በአንድ ላይ ሆነው ልጆችን ማሳደግና በመሬት ላይ ደግሞ የመግዛት ሥልጣን ተሰጣቸው - ይህ አስገራሚ ነገር ነው!

ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር አምላክ “ሰው ብቻውን መሆኑ መልካም አይደለምና የሚስማማውን ረዳት አበጅለታለሁ” አለ (ዘፍጥረት 2፡18)።

“ረዳት” ወይም “ኤዜር” የሚለው ቃል በአብዛኛው ትክክለኛ ባልሆነ መንገድ በመተርጎም ሴቶች ወንዶችን ለማገልገልና ለእነርሱ ለመገዛት የተፈጠሩ እንደሆኑ እንዲታሰብ ሲያደርግ ቆይቷል። ሊንዳ ብልቪዝል “በብሉይ ኪዳን ውስጥ በሌሎች ሥፍራዎች የተጠቀሰው ‘ኤዜር’ የሚለው ቃል አንድ ኃይል/ጉልበት ያለው አካል ለሌላው ድጋፍ ለሚፈልገው አካል የሚሰጠው እርዳታን ያመለክታል፤ ይህ እርዳታ ከእግዚአብሔር፣ ከንጉሥ፣ ከወዳጅ ወይም ከጦር ሠራዊት የሚሰጥ የኃይል ድጋፍን ያሳያል። ከዚህም በላይ ከአሥራ ዘጠኙ አሥራ አምስቱ ደግሞ እግዚአብሔር ብቻ የሚሰጠውን እርዳታ የሚያሳዩ ናቸው” በማለት ተናግረዋል፡ ፡(1). ለምሳሌ ያህል:

## ጥያቄ

መጽሐፍ ቅዱስ ሴቶች ለባሎቻቸው ረዳቶች እንደሆኑ ይናገራል። እንዲህ ከሆነ ወንዶች መሪዎች ሆነው የተፈጠሩ አይደሉምን?

## መልስ

ወንዶችና ሴቶች የተፈጠሩት አጋሮች እንዲሁም ለእግዚአብሔር መንግሥት እኩል ኃላፊነት እንዲኖራቸው ነው።

> አይኖቼን ወደ ተራሮች አነሣሁ፤ ረድኤቴ ከወዴት ይመጣል? ረድኤቴ ሰማይንና ምድርን ከፈጠረ፣ ከእግዚአብሔር ዘንድይመጣል (መዝሙር 121:1-2).

“ረዳት” ወይም “ኤዜር” የሚለው ቃል ፊት ለፊት፣ እኩል፣ የሚገጥም ማለት ነው፡፡ “የሚስማማውን ረዳት” ማለት በሁሉ ነገር ከእርሱ የምትገጥም አጋር ማለት ነው! ሴት የተፈጠረችው ከአዳም ጋር እኩል በሚያደርጋት ችሎታዎች በመሆኑ የእግዚአብሔር የሰጣቸውን ተልዕኮ መፈጸም ይችላሉ። እግዚአብሔር ወንዶችና ሴቶች እኩል አጋሮች ሆነው ጎን ለጎን ሆነው እንዲሠሩ ነው።

“ሥልጣን ያበላሻል፣ ፍጹም ሥልጣን ደግሞ ፍጹም ያበላሻል” ይባላል። አንድን ሰው (ወንድን) በሥልጣን ላይ ማስቀመጥ አደገኛ ነው። ይህ ኢፍትሐዊና ተጠያቂነት የሌለበት ዐይነት መሪነት ይሆናል። እግዚአብሔር ይህን ስለሚያውቅ የበላይና የበታች ሳይሆን አጋርነትን ለግንኙነታቸው መሠረት አደረገ። እግዚአብሔር በባልና ሚስት ግንኙነት መካከል ጤናማ ተጠያቂነት እንዲኖር ይፈልጋል። ከዚህ መስመር ፈቀቅ በማለት የበላይነትን በሌላው መጫን ለቃልና አካል ጥቃት ያጋልጣል። ስለዚህ ከእግዚአብሔር የመጀመሪያው አሠራር ጋር እንጣበቅ።

# ውድቀት

ሴቲቱንም እንዲህ አላት፤ "በምጥ ጊዜ ጭንቅሽን አበዛለሁ፤ በሥቃይም ትወልጃለሽ፤ ፍላጎትሽም ወደ ባልሽ ይሆናል፤ እርሱም የበላይሽ ይሆናል። አዳምንም እንዲህ አለው፦ "የሚስትህን ቃል ሰምተህ፣ 'ከእርሱ አትብላ' ብዬ ያዘዝሁህን ዛፍ በልተሃልና፣ ከአንተ የተነሣ ምድር የተረገመች ትሁን፤ በሕይወትህ ዘመን ሁሉ ምግብህን ጥረህ ግረህ ከእርሷ ታገኛለህ። ምድርም እሾኽና አሜከላ ታበቅልብሃለች፤ ከቡቃያዋም ትበላህ። ከምድር ስለተገኘህ፣ ወደ መጣህበት መሬት እስክትመለስ ድረስ እንጀራህን በፊትህ ላብ ትበላለህ። ዐፈር ነህና ወደ ዐፈር ትመለሳለህ።" (ዘፍጥረት 3:16-19).

## ጥያቄ

በብዙ ባሕሎች ውስጥ ወንዶች የበላይ ናቸው። ይህ የሆነው እግዚአብሐር በዚያ መንገድ ስለፈጠረ ነውን?

ወንድና ሴት ሁለቱም በውድቀት ተሳትፈዋል። ኀጢአትን መምረጣቸው እነዚህን ውጤቶች አምጥቷል፥ ከፉ የተፈጥሮ አካባቢ፣ በልጅ መውለድ ጊዜ መጨነቅና የወንድ የበላይነትን አስከተለ። ይህ እንድንኖረበት የተሰጠን መመሪያ አይደለም። ነገር ግን ኀጢአት ወደ ዓለም በመግባቱ ምክንያት የመጡ ከፉ ውጤቶች ናቸው። በማሳ ውስጥ እሾኽና አሜከላ ሲኖር እንደሚነቀሉ እንዲሁም የወንድ የበላይነትም ሊወገድ ይገባል እንጂ ተቀብለን ልንኖርበት አይገባንም። እንደ ብልቪዝል ገለጻ "የመለኮት ዓላማ የነበረው አጋርነት - አብሮ ምድርን መግዛት፣ ልጆችን ወልዶ ለማሳደግ የጋራ ኃላፊነት እንዲሁም በጋራ ሆነው ምድርን እንዲያርሱ ነበር፡ ፡ አንዱ በሌላው ላይ የበላይ መሆን የእግዚአብሔር ዓላማ አልነበረም። ይህ ለእግዚአብሔር ካለመታዘዝ የመጣ የግንኙነት ብልሹነት ነው" (2)። አሁንም ጎን ለጎን ማገልገል አለብን።

## መልስ

የወንድ የበላይነት ከሰው ልጅ በኀጢአት መውደቅ የመጣ መርገም ነው፣ ይህን ማሸነፍ እንጂ መቀበል ተገቢ አይደለም።

# በክርስቶስ አንድ ነን

## ጥያቄ

እግዚአብሔር ሰዎችን ሁሉ ይወዳል እንዲሁም ለሁሉም ሰው ዋጋ ይሰጣል፤ ነገር ግን ወንዶችና ሴቶች የሚና ልዩነት አይኖራቸውምን?

## መልስ

የሰዎች ሚና በስጦታ፣ በችሎታና በልምድ ላይ እንጂ በሥርዓተ ጾታ ላይ መሠረት ያደረገ መሆን የለበትም።

> በአይሁድና በግሪክ፣ በባሪያና በነጻ ሰው፣ በውንድና በሴት መካከል ልዩነት የለም፤ ሁላችሁም በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ናችሁ (ገላትያ 3:28).

አንዳንድ ሰዎች ይህ ክፍል ወንዶችና ሴቶች እኩል መወደዳቸውን፣ ዋጋ እንዳላቸውና መዳናቸውን (ሰብዓዊ እኩልነታቸውን) ይናገራል ይላሉ። ነገር ግን ሁለቱ የተለያየ ሥራ (እኩል ያልሆነ ሚና) እንዳላቸው ይረዳሉ።

በሚናዎች ውስጥ አንዱ ለሌላው የሚገዛበት ሁኔታ ይታያል፣ ለምሳሌ መምህር/ተማሪ ወይም አሠሪ/ሠራተኛ። እነዚህ ሚናዎች ግን በችሎታ ላይ የተመሠረቱ እንዲሁም ጊዜያዊ ናቸው። ተማሪ በክፍል ውስጥ ለመምህር ይገዛል ምክንያቱም መምህሩ ችሎታ አለው፣ ነገር ግን ይህ ለጊዜው ነው። መምህሩ ተማሪው ባለቤት በሆነበት ምግብ ቤት ውስጥ የሚሠራ ከሆነ፣ እነዚህ ሚናዎች ይለወጣሉ። ሚናዎች እንደ ሁኔታዎችና የሰዎች ብቃት በየጊዜው ይለዋወጣሉ።

ርብቃ ሚሪል ግሮቱይስ የሴት ለወንድ መገዛት በችሎታ ላይ የተመሠረተ ሳይሆን ሴት ከመሆን ማንነት ጋር የተያያዘ እንደሆነ ይገልጻሉ። ይህ ጊዜያዊ አይደለም፤ ሴት ልጅ አድጋ ከዚህ መውጣት የምትችልበት ሁኔታ የለም። ይህ በሚና እኩል ካለመሆንም አልፎ በማንነትም እኩል አለመሆንን ያመለክታል። ሴት ምንም ያህል ችሎታ ብኖራት በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ ለወንዶች ሥልጣን መገዛት አለባት፣ ነገር ግን በተመሳሳይ ሁኔታ ደግሞ ከወንዶች እኩል ዋጋ አላት የሚለው ሐሳብ ምክንያት የለሽ ክርክር ነው። (3).

ይህ ጥቅስ ስለወንዶችና ሴቶች ብቻ ሳይሆን ሚና በዘርና በመደብም የሚወሰን መሆኑን ይናገራል!

ጳውሎስ ሁላችንም አንዱ የሌላው ግልባጭ የሆንን ተመሳሳይ “ወጥ-ጾታ” እንደሆንን አይናገርም። ይህ ጥቅስ ለሁሉም እኩል በሆነው በክርስቶስ ሥራ ውስጥ ዘር፣

መደብና ሥርዓተ-ጾታ አስፈላጊ እንዳልሆነ ያውጃል። ብዙ የአዲስ ኪዳን ክፍሎች አማኞች ሁሉ በማንነትና በሚና እኩል እንደሆኑ ያረጋግጡልናል፡ (ዮሐንስ 17:20-23፤ ሮሜ 12:4-5፤ 1 ቆሮንቶስ 12:12-14፤ ኤፌሶን 4:4-8, 11-13)።

በዚህ በተከፋፈለ ዓለም ውስጥ ቤተክርስቲያን በአንድነት አርዓያ መሆን አለባት። በማንኛውም መንገድ ሴቶች ከወንዶች "ያነሱ" እንደሆኑ መልዕክት የሚያስተላልፍ ቃል፣ አመለካከት ወይም መመሪያ እግዚአብሔር ለሰዎች ሁሉ ያሳየውን ፍቅር እንዳናሳይ መሰናክል ይሆንብናል።

> በጌታ ዘንድ ግን ሴት ያለወንድ፣ ወንድም ያለ ሴት አይሆንም። ሴት ከወንድ እንደ ተገኘች ሁሉ፣ ወንድም ከሴት ይወለዳልና፤ ነገር ግን የሁሉም መገኛ እግዚአብሔር ነው። (1 ቆሮንቶስ11:11-12).

በአሁኑ ዘመን ኅብረተሰብ ውስጥ ሴቶችና ወንዶች የበሰለ ውሳኔ ለመስጠት እኩል መብትና አቅም እንዳላቸው ይታሰባል። አንዲት ችሎታ ያላት ሴት የአእምሮ የማሰብ ብቃቷ ተጠቅማ የበሰሉ ውሳኔዎች እንዳትወስን ማድረግ እርሷንና ከእርሷ አካባቢ ያሉት ሴቶች ሁሉ ማዋረድ ነው። ከመጀመሪያው የነበረው የእግዚአብሔር ሐሳብ ወንዶችና ሴቶች እርስ በርስ በመነጋገር በጋራ ሥልጣን የጋራ ውሳኔ እንዲወስኑ ነው። ጎን ለጎን ሆነን ማገልገል አለብን።

አንዳንድ ጊዜ ውይይቶች ወደ ውሳኔ ላያደርሱ ይችላሉ። ባልና ሚስት ተነጋግረው ውሳኔ ላይ መድረስ ያቅታቸዋል። ግልበርት ብለዝኪአን ለዚህ ሊረዱ የሚችሉ የመፍትሔ መንገዶች አቅርበዋል (እነዚህ በቅደም ተከተል የተጠቀሱ አይደሉም)፡

1. የእግዚአብሔርን ምሪት መፈለግ
2. አንዱ ለሌላው መገዛት፣ መደማመጥ፣ መከባበር እና አንዱ የራሱን ትቶ በሌላው ሰው ቦታ በመሆን ነገሮችን ማሰብ መቻል
3. በክርክሩ ጉዳይ ላይ እያንዳንዱ መንፈሳዊ ስጦታዎችን፣ የተፈጥሮ ችሎታዎችና ሙያውን ይጠቀም
4. ማመቻመች
5. ከሌሎች ታማኝና ልምድ ካላቸው ሰዎች ምክር መጠየቅ
6. መጽሐፍ ቅዱሳዊ መርሆዎችን መፈለግ/መግለጽ
7. የአማራጭ ሐሳቦችን ጥቅምና ጉዳት ለይቶ ማውጣት
8. ጉዳዩ ይበልጥ የሚመለከተው ሰው በውሳኔው ላይ የበለጠ ድርሻ እንዲኖረው መፍቀድ (4).

## ጥያቄ

ውሳኔዎችን ለመወሰን አንድ ሥልጣን ያለው ሰው መኖር አለበት። ይህ ሰው በተፈጥሮ ራሱ ወንድ መሆን የለበትምን?

## መልስ

ተጠያቂነት እንዲኖር እንዲሁም የሌላውን ዕውቀትና ልምድ ለመጠቀም እንዲያስችል ውሳኔዎች በጋራ ሊሰጡ ይገባቸዋል።

## ጥያቄ

በብሉይ ኪዳን ካህናት የሚሆኑት ወንዶች ብቻ ነበሩ፤ ስለዚህ ባሎች ካህናት ወይም የቤተሰብ መንፈሳዊ መሪዎች አይደሉምን?

## መልስ

እያንዳንዱ ሰው ወደ እግዚአብሔር ለመቅረብ እኩል ዕድል እንዲሁም በእግዚአብሔር ፊት እኩል ኃላፊነት አለው።

> እናንተ ግን ከጨለማ ወደ አስደናቂ ብርሃኑ የጠራችሁን የእግዚአብሔርን ታላቅ ሥራ እንድታውጁ፣ የተመረጠ ትውልድ፣ የንጉሥ ካህናት፣ ቅዱስ ሕዝብ፣ እግዚአብሔር የለያችሁ ሕዝብ ናችሁ። (1 ጴጥሮስ 2:9)

በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ባል የቤተሰብ ካህን እንደሆነ የሚናገር ክፍል የለም፡፡ በክርስቶስ አማካኝነት ሁሉም ወደ እግዚአብሔር ለመቅረብና በእርሱ ፊት እኩል ኃላፊነት አላቸው። ጆን ፊላን እንደተናገሩት “የቤተመቅደሱ መጋረጃ ለሁለት ተቀደደ፤ አሁን ሰዎች ሁሉ ወደ እግዚአብሔር የመቅረብ ዕድል አላቸው፡፡ የእግዚአብሔር ሰዎች ሁሉም ካህናት ናቸው። የእግዚአብሔር ሰዎች ሁሉም ቅዱሳን ናቸው። የእግዚአብሔር ሰዎች ሁሉም መንፈስ ቅዱስ አላቸው” (5).

“አባት” እግዚአብሔርን ለመግለጽ በጥቅም ላይ ከዋሉ ብዙ ተምሳሌት መካከል አንዱ ነው። ይህ በዚያን ዘመን ውርስን የሚሰጥና ጥበቃ የሚያደርግ ሰውን ያሳያል፡፡ እግዚአብሔር ወንድ አይደለም። እግዚአብሔር መንፈስ ነው (ዮሐንስ 4:24)። ሴቶችና ወንዶች ሁለቱም በእግዚአብሔር መልክ የተፈጠሩና እኩል እግዚአብሔርን የሚያንጸባርቁ ናቸው። ማይሚ ሐዳድ እንዲህ ብለዋል፤ “እግዚአብሔር ወንድ እንደሆነ ማሰብ የጣዖት አምልኮ ነው፣ እግዚአብሔርን በመልካችን መፍጠራችን ነው፤ ይህ ደግሞ ከቅዱሳት መጻሕፍት ትምህርት ጋር ይቃረናል” (6).

## ጥያቄ

እግዚአብሔር አባታችን ስለሆነ እንዲሁም ኢየሱስ ወንድ ስለነበረ፣ ወንዶች መንፈሳዊ መሪዎች መሆን አይገባቸውምን?

## መልስ

እግዚአብሔር ወንድ አይደለም። እግዚአብሔር መንፈስ ነው፤ ወንድና ሴት ሁለቱም የእርሱን መልክ ያንጸባርቃሉ።

ኢየሱስ ወደዚህ ዓለም የመጣው ወንድ ሆኖ ነበር፤ ይህም ሴቶች መስበክ በማይችሉበት በቤተመቅደስ ውስጥ መስበክ እንዲችል ነበር። በዚያን ጊዜ ሴቶች ወደ ቤተመቅደስ መግባት ብችሉም መስበክ ግን አይችሉም ነበር። ክርስቶስ የወንድን ሳይሆን የሰውን አካል ለብሶ እኛን አዳነን።

> አንድ ሰው ብቸኛውን ቢያጠቃውም፣ ሁለት ከሆኑ ይመክቱታል፣ በሦስት የተገመደ ገመድም ቶሎ አይበጥስም (መክብብ 4:12).

አንዱን ገመድ ብናላላው፣ ገመዱ ጥንካሬ አይኖረውም። እውነተኛ ጤናማ የሆነ ግንኙነት እርስ በርስ መከባበር ያለበት ነው። አባትና እናት ለቤተሰባቸው እጅግ መልካም የሆነውን ለመምረጥ የጋራ ኃላፊነት ካላቸውና ውሳኔዎችን በጋራ ከወሰኑ ልጆቻቸው እጥፍ ተጠቃሚዎች ይሆናሉ። ወላጆች የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንዲፈልጉ ማበረታታት ልጆቻቸው በቤት ውስጥ አይደሰቱም ወይም ቅድሚያ አይሰጣቸውም ማለት አይደለም። ወላጆች በፈቃደኝነት አንዱ የሌላውን ሥራ በቤት ውስጥ ወይም በውጭ ሥራ ወይም በሁለቱም መደገፍ መልካም አርዓያነት ያለው ኑሮ ነው።

ሦስተኛው ገመድ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። እርሱ የቤታችን ጌታ ነው። ክርስቶስ ክብር ባገኘበት ቤት ውስጥ ሁሉም እርስ በርስ ይከባበራል፣ ፍቅርም ይበዛል።

በአንዳንድ ቦታዎች ግን በቤት ውስጥ እናት ወይም አባት ላይኖሩ እንደሚችሉ መገንዘብ አለብን። በእነዚህ ሁኔታዎች ውስጥ መድልዎ ማድረግና የተለመደውን ባሕላዊ ሚና እንዲይዙ ማድረግ አይጠቅምም። የክርስቶስ አካል ሁሉ እነዚህን ቤተሰቦች መረዳትና መደገፍ አለበት።

## ጥያቄ

ለልማዳዊው ሚናዎች የማንታዘዝ ከሆነን ቤተሰብን ማፈራረሳችን ነው ብለው ለሚናገሩ ሰዎች እንዴት ምላሽ ትሰጣላችሁ?

## መልስ

መጽሐፍ ቅዱሳዊ እኩልነት ተግባራዊ የሚደረግበት ቤተሰብ ይጠናከራል እንጂ አይፈርስም።

# ኢየሱስና ሴቶች

## ጥያቄ

ኢየሱስ ሴት ደቀመዛሙርትን ለምን አልመረጠም?

## መልስ

በዚያን ጊዜ ተልዕኮውን እንዲፈጽሙ ወንድ አይሁዶች ተመረጡ። አሁን ግን ለታላቁ ተልዕኮ ስኬት ሁሉም ተጠርተዋል።

> ከእርሱ ጋር እንዲሆኑ፣ ለስብከትም ይልካቸው ዘንድ ዐሥራ ሁለቱን ሾማቸው፤ ሐዋርያትም ብሎ ጠራቸው። አጋንንትን እንዲያስወጡም ሥልጣን ሰጣቸው። (ማርቆስ 3:14-15)

ሪቻርድና ካትሪን ክሮግር እንዲህ ገልጸዋል፤ "ኢየሱስ ከእርሱ ጋር በመሄድ በስብከት ተልዕኮው የሚያገለግሉት ሴቶች ነበሩት። ነገር ግን በዚያን ዘመን ሴቶች ብቻቸውን በመሄድ በአደባባይ እንዲሰብኩና የፈውስ ተልዕኮን እንዲፈጽሙ መላክ የማይቻል ነበር። የታልሙድ ልቃውንት በአደባባይ ከሴቶች ጋር፣ ሚስቶቻቸው ቢሆኑም እንዳያወሩ ተነግሮአቸዋል። ስለእግዚአብሔር ነገርም ከሴቶች ጋር መነጋገር ክልክል ነበር። ይህ ለኀጢአት ፈተና ራስን ማጋለጥ እንደሆነ ይታሰባል ....። ኢየሱስ ይህ አመለካከት ከመለወጡ በፊት ሰዎቹ መለወጥ እንዳለባቸው ያምናል።" (7)

ሌላው ማስታወስ የሚገባን ነገር በደቀመዛሙርቱ መካከል ከአሕዛብ ወገን የሆነ ሰው አለመኖሩን ነው። እንግዲህ ደቀመዛሙርት የቤተክርስቲያን አመራር ሞዴል ከሆኑ፣ አይሁዳውያን ያልሆኑ ወንዶች ሁሉ ከአመራር መውጣት አለባቸው ማለት ነው።

### ሴት ደቀመዝሙር

> ከዚህ በኋላ ኢየሱስ የእግዚአብሔርን መንግሥት የምሥራች ቃል እየሰበከ በየከተማውና በየመንደሩ አለፈ። ዐሥራ ሁለቱም ከእርሱ ጋር ነበሩ፤ እንዲሁም ከርኩሳን መናፍስትና ከደዌ የተፈወሱ አንዳንድ ሴቶች አብረውት ነበሩ፣ እነርሱም ሰባት አጋንንት የወጡላት መግደላዊት የተባለችው ማርያም፣ የሄሮድስ ቤት ኀላፊ የነበረው የኩዛ ሚስት ዮሐና፣ ሶስና፣ ደግሞ ሌሎች ብዙዎች ነበሩ፤ እነዚህም በግል ንብረታቸው የሚያገልግሎት ነበሩ። (ሉቃስ 8:1-3)

የሕዝብ ስብሰባዎች በሚኖሩበት ጊዜ ሴቶች አይቆጠሩም ነበር፤ ነገር ግን ኢየሱስ የእነርሱን አገልግሎትና የገንዘብ ድጋፍ ይቀበል ነበር።

## ኢየሱስ ሴቶችን ያስተምራል

> ኢየሱስና ደቀመዛሙርቱ መንገድ ሲሄዱ፣ ኢየሱስ ወደ አንድ መንደር ገባ፣ ማርታ የተባለች አንዲት ሴትም በቤቷ ተቀበለችው። እርሷም ማርያም የተባለች እህት ነበረቻት፤ ማርያምም ቃሉን እየሰማች በጌታ እግር ሥር ተቀምጣ ነበር። ማርታ ግን በሥራ ብዛት ትባክን ነበርና ወደ እርሱ ቀርባ፣ "ጌታ ሆይ፣ እህቴ ሥራውን ለእኔ ብቻ ጥላ ስትቀመጥ ዝም ትላለህን? እንድታግዘኝ ንገራት እንጂ" አለችው። ጌታ ግን እንዲህ ሲል መለሰላት፤ "ማርታ፣ ማርታ፤ ስለብዙ ነገር ትጨነቂያለሽ፣ ትዋከቢአለሽም፤ የሚያስፈልግ ግን አንድ ነገር ብቻ ነው፤ ማርያም እኮ የሚሻለውን ድርሻ መርጣለች፤ ይህም ከእርሷ አይወሰድም" (ሉቃስ 10:38-42)

በኢየሱስ ዘመን ሴቶች ከብዙ ዐይነት የትምህርት ዕድል የተከለከሉ ነበሩ። ነገር ግን ማርያም በእርሱ እግር ሥር የደቀመዝሙር ሥፍራን ስትወስድ የመማር መብት እንዳላት ተሟገተላት። ኢየሱስ ስለእርሷ ምርጫ ሲናገር፥ "ይህም ከእርሷ አይወሰድም" አለ። ብዙዎች ግን ይህን ከእርሷ ለመውሰድ ሙከራ አድርገው ነበር።

## ወንጌላዊ የሆነች ሴት

> በዚያን ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ተመልሰው መጡ፤ ከሴት ጋር ሲነጋገር በማግኘታቸውም ተደነቁ፤ ሆኖም ግን፣ "ምን ፈለግህ?" ወይም "ከእርሷ ጋር የምትነጋገረው ለምንድነው?" ብሎ የጠየቀው ማንም አልነበረም። ሴትዮዋ እንስራዋን ትታ ወደ ከተማ ተመለሰች፤ ሕዝቡም፣ "ያደረግሁትን ሁሉ የነገረኝን ሰው ኑና እዩ፤ እርሱ ክርስቶስ ይሆን እንዴ?" አለች፤ እነርሱም ከከተማ ወጥተው እርሱ ወዳለበት አመሩ። ... ሴትዮዋ "ያደረግሁትን ሁሉ ነገረኝ" ብላ ስለ መሰከረች፣ ከዚያች ከተማ ብዙ ሳምራውያን ወደ እርሱ በመጡ ጊዜ አብሮአቸው እንዲቆዩ አጥብቀው ለመኑት፤ እዚያም ሁለት ቀን ቆየ። "ከቃሉም የተነሣ ሌሎች ብዙዎች አመኑ።" (ዮሐንስ 4:27-30, 39).

### ጥያቄ

በኢየሱስ አገልግሎት ውስጥ ሴቶች ተሳትፈው ነበርን?

### መልስ

በኢየሱስ አገልግሎት ውስጥ ሴቶች ይሳተፉ ነበር። ኢየሱስ ለሴቶች የነበረው አክብሮትና እነርሱን በአገልግሎቱ ውስጥ ማካተቱ እጅግ ተራማጅ ውሳኔ ነበር!

ሴቶችን በአደባባይ ከማየት መራቅና ለኀጢአት ፈተና የሚያጋልጡ እንደሆኑ ይታይ ነበር። ነገር ግን ኢየሱስ መልካም ስም ከሌላት ሴት ጋር በውኃ ጉድጓድ አጠገብ ቆሞ ማውራቱ ደቀመዛሙርቱን አስደንግጧል። ይህ ኢየሱስ ከአንድ ሰው ጋር ከተነጋገራቸው ንግግሮች መካከል በወንጌል ከተጻፉት ሁሉ ትልቁ ነው፡፡ ከዚያም በኋላ ኢየሱስ ወደ ከተማዋ በመሄድ ለገዛ ሰዎችዋ ሰባኪ እንድትሆን ላካት። ከእርሷ ምስክርነት የተነሣ ብዙ ሰዎች በኢየሱስ አመኑ።

## ኢየሱስ ቅድሚያ ማግኘት ያለበትን አስታወቀ

> ኢየሱስ ይህን እየተናገረ እያለ ከሕዝቡ መካከል አንዲት ሴት ድምጽዋን ከፍ አድርጋ "የተሸከመችህ ማሕፀንና የጠባሃቸው ጡቶች ብፁዓን ናቸው" አለችው። እርሱ ግን ብፁዓንስ የእግዚአብሔር ቃል ሰምተው የሚታዘዙት ናቸው" አለ (ሉቃስ 11:27-28).

ሴቶች በአብዛኛው ልጆችን በመውለድና በማሳደጋቸው ዋጋ ይሰጣቸው ነበር፣ ኢየሱስ ግን ትልቁ ነገር የእርሱ ደቀመዝሙር መሆኑን ተናገረ።

## ሴቶች ለደቀመዛሙርቱ ስለትንሳኤ ተናገሩ

> ሴቶቹም በፍርሀትና በደስታ ተሞልተው ለደቀመዛሙርቱ ለመንገር በፍጥነት እየሮጡ የመቃብሩን ስፍራ ትተው ሄዱ። ወዲያው ኢየሱስ አገኛቸውና፣ "ሰላም ለእናንተ ይሁን!" አላቸው። እነርሱም ወደ ኢየሱስ ቀርበው እግሩን ይዘው ሰገዱለት። ኢየሱስም፣ "አትፍሩ፤ ሂዱና ወደ ገሊላ እንዲሄዱ ለወንድሞቼ ንገሯቸው፤ በዚያ ያዩኛል" አላቸው (ማቴዎስ 28፥8-10)

በዚያን ዘመን በፍርድ ቤት የሴት ምስክርነት ተቀባይነት አልነበረውም፤ ነገር ግን ኢየሱስ ግን ሁለት ሴቶች ስለትንሣኤው እንዲመሰክሩና እንዲያውጁ መረጣቸው።

ኢየሱስ ስለሴቶች መገዛት በፍጹም አላስተማረም። እርሱ በሰው ልጅ ውድቀት የደረሰውን ውጤት ለመቀልበስ ወደ ዓለም መጣ። ኢየሱስ ለሴቶች የነበረው አመለካከትም ይህን ይገልጽ ነበር። ኢየሱስ ሴቶችን ከኀጢአትና ከሚደርስባቸው አድልዎ አርነት አወጣቸው!

# መንፈሳዊ ስጦታዎች

…በነቢዩ በኢዩኤል እንዲህ ተብሎ የተነገረ ነው፤ "እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤ በመጨረሻው ቀን፣ መንፈሴን በሥጋ ለባሽ ሁሉ ላይ አፈሳለሁ፤ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችሁ ትንቢት ይናገራሉ፣ ጎልማሶቻችሁ ራእይ ያያሉ፣ ሽማግሌዎቻችሁ ሕልም ያልማሉ። በዚያን ጊዜ በወንዶችና በሴቶች አገልጋዮቼ ላይ መንፈሴን አፈሳለሁ፣ እነርሱም ትንቢት ይናገራሉ" (የሐዋርያት ሥራ 2:16-18)።

ነገር ግን መንፈስ ቅዱስን መግለጥ ለእያንዳንዱ ሰው የሚሰጠው ለጋራ ጥቅም ነው። … እነዚህ ሁሉ የዚያው የአንዱ መንፈስ ስጦታዎች ሲሆኑ፣ ለእያንዳንዱ ሰው እርሱ ራሱ እንደ ፈቀደ ይሰጠዋል" (1 ቆሮንቶስ 12:7፣11)።

እንደ ተሰጠን ጸጋ የተለያዩ ስጦታዎች አሉን፣ ለአንዱ የተሰጠው ስጦታ ትንቢት መናገር ከሆነ፣ እንደ እምነቱ መጠን ይናገር። ማገልገል ቢሆን ያገልግል፤ ማስተማርም ከሆነ ያስተምር፤ መምከር ከሆነ ይምከር፤ ለሌላቸው መለገስ ከሆነም አብዝቶ ይለግስ፤ ማስተዳደር ከሆነም በትጋት ያስተዳድር፤ ምሕረት ማድረግ ከሆነም በደስታ ይማር" (ሮሜ 12:6-8).

እንደ ታማኝ የእግዚአብሔር ልዩ ልዩ ጸጋ መጋቢ እያንዳንዱ ሰው በተቀበለው የጸጋ ስጦታ ሌላውን ያገልግል" (1 ጴጥሮስ 4:10)።

በአዲስ ኪዳን ውስጥ ስጦታዎች በተጠቀሱ ቁጥር ሥርዓተ ጾታን መሠረት ያደረገ ልዩነት መኖሩ አልተጠቀሰም። ልዩነት ሥልጣንን በሚያሳዩ ስጦታዎችም ላይ አልተደረገም። የሕዝቡ ግማሽ ቁጥር የሆኑ ሴቶች እግዚአብሔር በሰጣቸው ስጦታ በነጻነት እንዳያገለግሉ መከልከል ማለት ለወንጌል ሥራ ከፍተኛ መሰናክል መፍጠር ነው።

## ጥያቄ

እግዚአብሔር አማኞች መንፈሳዊ ስጦታዎችን ይሰጣል፣ እነዚህ ስጦታወች ለወንድና ሴት ልዩ ናቸው አይደለም?

## መልስ

እግዚአብሔር መንፈሳዊ ስጦታዎችን እንደፈለገ ይሰጣል፤ ስጦታዎች የሚሰጡት ሥርዓተ ጾታን መሠረት በማድረግ አይደለም።

ኢየሱስ (በማቴዎስ 9:37-38) ላይ እንዲህ ብሎ ተናገሯል፡ "…መከሩ ብዙ ነው፤ የመከሩ ሠራተኞች ጥቂቶች ናቸው፤ ስለዚህ የመከሩ ጌታ፣ ወደ መከሩ ሠራተኞችን እንዲልክ ለምኑት።" ስለዚህ ማንም ሰው የእግዚአብሔር ሕዝብ እንዳያገለግል ለምን መናከል ይፈጥራል?

በ2004 (እአአ) በታይላንድ በተካሄደው የላውሳኔ ኮሚቴ ለዓለም የወንጌል ሥርጭት መድረክ ላይ ከ130 ሀገሮች የተወጣጡ 1530 ተሳታፊዎች ተገኝተው ነበር። ዋና ዓላማቸው "ቤተክርስቲያንን ሁሉ ሙሉ ወንጌል በመያዝ ወደ ዓለም ሁሉ መሄድ እንድትችል እንዴት ማነሳሳት" እንደሚቻል መወያየት ነበር። በዚያ ላይ ከወጡ የአቋም መግለጫዎች መካከል አንዱ እንዲህ ይላል "እኛ አማኞች ሁሉ ካህናት እንደሆኑ እናምናለን። ስለዚህ ቤተክርስቲያን ሴቶችን፣ ወንዶችንና ወጣቶችን በዓለም አቀፍ ደረጃ ላይ ለሚካሄደው የወንጌል ሥርጭት ምስክሮችና አብሮ ሠራተኞች እንዲሆኑ እንድታስታጥቃቸው፣ እንድታበረታታቸውና እንድታጎለብታቸው ጥሪ እናደርጋለን" (8)።

ግልበርት ብሊዘኪአን ይህን በግልጽ እንዲህ በማለት ገልጾታል፡ "ጌታችን ኢየሱስ መክሊታቸውን ለእግዚአብሔር መንግሥት አገልግሎት ጥቅም በሚሰጥ መንገድ ሳይጠቀሙ ቀርተው የቀበሩ አገልጋዮች የደረሰባቸውን ክፉ ውጤት ተናግሯል (ማቴዎስ 25:30)። ምዕመናን እግዚአብሔር የሰጣቸውን ችሎታዎች ለእግዚአብሔር መንግሥት ዓላማ እንዳይጠቀሙ ጸጋቸውን እንዳያወጡ የሚያፍኑ የቤተክርስቲያን መሪዎች እጅግ በጣም የሚያስደነግጥ የእግዚአብሔር ፍርድ ይጠብቃቸዋል" (9)።

# ሴቶች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ

ቅዱሳት መጻሕፍት ብዙ ሴት መሪዎች እንደነበሩ ይገልጻል። በዚያን ጊዜ ከነበረው የባሕል ተጽዕኖ ምክንያት የወንዶቹ ያህል አልተጠቀሱም። ነገር ግን ሴቶች መምራታቸው ወይም ማስተማራቸው ስህተት ቢሆን ኖሮ መሪዎች ወይም አስተማሪዎች ሆነው ባልተሾሙ/ባልተመረጡ ነበር።

- ሐና (ሉቃስ 2:36-38)፣ እና የፊልጶስ አራት ሴት ልጆች (የሐዋርያት ሥራ 21:8-9) ነቢያት ነበሩ።
- ጵርስቅላ ከአቂላ ጋር በመሆን ለአጵሎስ የእግዚአብሔርን መንገድ በይበልጥ አስተማሩ (የሐዋርያት ሥራ 18:24-26)፣ በቤታቸው ቤተክርስቲያንን መሠረቱ (1ቆሮንቶስ 16:19) እንዲሁም ጳውሎስ አብረውኝ ለሚያገለግሉ ብሎ ስለእነርሱ ተናግሯል (ሮሜ 16:3).
- ፊቤን ዲያቆንና የጳውሎስ ደጋፊ ነበረች (ሮሜ16:1-2)።
- ልድያ በቤቷ ውስጥ ከምዕመናን ጋር ትሰበሰብ ነበር፣ ጳውሎስና ሲላስንም ወደ ቤቷ ተቀበለች (የሐዋርያት ሥራ 16:13-15፣40)።
- ዩልያን ሐዋርያ ነበረች (ሮሜ 16:7)።
- ኤዎድያን እና ሲንጤኪን ከጳውሎስ ጋር የሚያገለግሉ ነበሩ (ፊልጵስዩስ 4:2-3)።

## ጥያቄ

በመጀመሪያዋ ቤተክርስቲያን ውስጥ የነበሩ መሪዎች ሁሉ ወንዶች አልነበሩምን?

## መልስ

በዚያን ጊዜ ከነበሩ የማሕበራዊ ሁኔታዎች አንጻር በአዲስ ኪዳን ውስጥ በሚያስደንቅ ሁኔታ ብዙ ሴት መሪዎች ነበሩ።

# ዝምታ

## ጥያቄ

መጽሐፍ ቅዱስ ሴት በቤተክርስቲያን ውስጥ አትናገር ይላል አይደለምን?

## መልስ

በቆሮንቶስ ቤተክርስቲያን ውስጥ ሴቶች ዝም ማለት አለባቸው የሚለው በዚያን ወቅት የነበረ ሥርዓት ነው፡፡ በዚህ ዘመን ካለው የሴቶች ችሎታና ትህትና ጋር ምንም ዐይነት ግንኙነት የለውም።

> ... ይህ ሁሉ ግን ለማነጽ ይሁን። በልሳን የሚናገር ቢኖር፣ ሁለት ወይም ቢበዛ ሦስት በየተራ ይናገሩ፤ ሌላው ደግሞ ይተርጉም፣ የሚተረጉም ሰው ከሌለ ግን በጉባኤ መካከል ዝም ይበልና፣ ለራሱና ለእግዚአብሔር ይናገር፡፡ ሁለት ወይም ሦስት ነቢያት ይናገሩ፤ ሌሎቹ ደግሞ የተነገረውን በጥንቃቄ ይመዝኑ። ከተቀመጡትም መካከል አንዱ ሰው አንድ ነገር ቢገለጥለት፣ የመጀመሪያው ተናጋሪ ዝም ይበል። ... እግዚአብሔር የሰላም አምላክ እንጂ የሁከት አምላክ አይደለም። በቅዱሳን አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ እንዲሁ ነው፤ ሴቶቹ በጉባኤ ዝም ይበሉ፤ ሕግም እንደሚለው እንዲታዘዙ እንጂ እንዲናገሩ አልተፈቀደላቸውም። ሴቶች ለማወቅ የሚፈልጉት አንዳንድ ነገር ካለ፣ ባሎቻቸውን በቤት ይጠይቁ፤ ምክንያቱም ሴት በጉባኤ መካከል ብትናገር የሚያሳፍር ነው (1ቆሮንቶስ 14:26-30፣33-35)።

በ21ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ሴት በጉባኤ መናገር የሚያሳፍር አይደለም። ይህ አሁን አይሠራም። ብዙ ሰዎች በእምነታቸው ያላደጉት ክርስትና የወንድ የበላይነት የሚታይበት ሃይማኖት እንደሆነ በማሰባቸው ነው።

የዚህ የቆሮንቶስ መጽሐፍ ምንባብ የሚናገረው የአማኞች አምልኮ ሥርዓት ያለው መሆን አለበት የሚለውን መርህ ሐሳብ ነው። ዝም እንዲሉ የተጠየቁት ሴቶች ብቻ እንዳልሆኑ አስተውሉ። ማንም በልሳን መናገር የሚፈልግ፣ ተርጓሚ ከሌለ ዝም ማለት አለበት። አንድ ነቢይ እየተናገረ እያለ፣ አዲስ ነገር ለሌላ ነቢይ ከተገለጠለት ደግሞ የመጀመሪያው መናገሩን ማቆም አለበት። አምልኮው ሥርዓት ያለው ሊሆን ይገባል ምክንያቱም እግዚአብሔር የሰላም አምላክ ነው።

ክራግ ኬነር እንዲህ ብለው ጽፈዋል፡ "በጥንቱ የሜድተራንያን ሀገሮች አካባቢ ሴቶች በማያውቁት ሰዎች ፊት አይናገሩም ነበር... ሴቶች በአማካይ እንደ ወንዶቹ የተማሩ አልነበረም፣ ስለዚህ የጥናታዊ ጽሑፎች ዕውቀት አልነበራቸውም። ... ጳውሎስ ሴቶች በጉባኤ መካከል ወንዶችን በመጠየቅ የነበረውን ማሕበራዊ

ሥነምግባር እንዳያበላሹ መከራቸው እንጂ የእነርሱን መማር አልተቃወመም። ... ዕውቀታቸው በጨመረ መጠን ደግሞ በሚጸልዩበትና ትንቢት በሚናገሩበት ጉባኤ ውስጥ አሳባቸውን በተሻለ ሁኔታ ለመግለጽ የአእምሮ ብቃት ይኖራቸዋል። ከዚህ አንጻር ሲታይ ዋናው ጉዳይ ሥርዓተ ጾታ ሳይሆን በትሕትና መኖርና መማር ነው፥ ፥ እነዚህ ሁለቱ ደግሞ ሴቶች በአሁኑ ጊዜ በቤተክርስቲያን እንዳይናገሩ እንቅፋት ሊሆኑ የሚችሉ ነገሮች አይደሉም” (10)።

ጳውሎስ ሴቶች በቤተክርስቲያን ውስጥ ሁልጊዜ ዝም እንዲሉ ለመናገር ፈልጎ ቢሆን ኖሮ ሦስት ምዕራፎችን ቀደም ብሎ (በ1ቆሮንቶስ11፥5) ላይ ሴቶች ስጸልዩ እና ትንቢት ስናገሩ ጸጉራቸውን መሸፈን እንዳለባቸው መመሪያ አይሰጥም ነበር።

# ሥልጣንና ማስተማር

## ጥያቄ

መጽሐፍ ቅዱስ ሴቶች ማስተማር ወይም በወንድ ላይ ሊሰለጥኑ አይገባም ብሎ ስለሚናገር፣ ሴቶች አስተማሪዎች ወይም መጋቢዎች መሆን የለባቸውም ማለት ነውን?

## መልስ

በኤፌሶን ቤተክርስቲያን ውስጥ የሴቶችን ሥልጣን የወሰነው ይህ ጥቅስ በዚህ ዘመን ተግባራዊ የሚሆነው ያልሰለጠኑ ሰዎች ሐሰተኛ ትምህርትን መዋጋት አይችሉም በሚለው ትርጉም ነው።

> ሴት በጸጥታና በሙሉ መገዛት ትማር። ሴት ዝም እንድትል እንጂ እንድታስተምር ወይም በወንድ ላይ ሥልጣን እንዲኖራት አልፈቅድም፡፡ ምክንያቱም አዳም ቀድሞ ተፈጥሮአል፣ ከዚያም ሔዋን ተፈጠረች፡፡ ደግሞም የተታለለው አዳም አይደለም፤ የተታለለችውና ኀጢአተኛ የሆነችው ሴቷ ናት፤ ይሁን እንጂ ሴት በእምነትና በፍቅር፣ በቅድስና ራሷን እየገዛች ብትጸና ልጅ በመውለድ ትድናለች (1 ጢሞቴዎስ 2:11-15).

በዚህ ክፍል ውስጥ የተነሳው መርህ ሐሰተኛ ትምህርትን መዋጋት ነው። ይህ ሁኔታ ደግሞ በጳውሎስ እንዲህ ተብሎ ተጠቅሷል፡

> ወደ መቄዶንያ በሄድሁ ጊዜ ዐደራ እንዳልሁህ፣ አንዳንድ ሰዎች ከእንግዲህ የሐሰት ትምህርት እንዳያስተምሩ ታዛቸው ዘንድ በዚያው በኤፌሶን ተቀመጥ (1ጢሞቴዎስ1፡3)።

ጳውሎስ ሴቶች የሐሰት ትምህርት አስተማሪዎች ትኩረትም እንደሆኑ ይናገራል፡

> እነርሱም በየቤቱ ሾልከው እየገቡ የኀጢአት ብዛት የተጫናቸውን፣ በተለያዩ ክፉ ምኞት ውስጥ ገብተው የሚዋልሉ መንፈስ ደካማ ሴቶችን የሚያጠምዱ ናቸው” (2 ጢሞቴዎስ 3:6)።

## “ሴት በዝግታ ትማር”

በዚህ ጥቅስ መጀመሪያ ላይ የተጻፉ ቃላት ግልጽና መሠረታዊ ቢሆኑም በአብዛኛው የሚዘለሉ ናቸው። ጳውሎስ ሴቶች መማር እንዳለባቸው ተናግሯል። በእርሱ እምነት የሐሰት ትምህርትን ለመዋጋት ከሁሉም የሚበልጠው ስልት ትክክለኛውን ትምህርት ማስተማር ነው። ስለዚህ ሴቶች እንደ ማንኛውም መልካም የአይሁድ ተማሪዎች በዝግታና መምህራኖቻቸውን በማክበር መማር ይኖርባቸዋል።

## “ሴት እንድታስተምር አልፈቅድም”

ጳውሎስ ማለት የፈለገው ሴቶች በበቂ ሁኔታ ሳይሰለጥኑ ማስተማር የለባቸውም ነው። ምክንያቱም እርሱ ራሱ የጵርስቅላን የማስተማር ብቃት ያደንቅ ነበር (የሐዋርያት *ሥራ* 18:24-26 እና ሮሜ 16:3-5)። ጵርስቅላ ከባሏ ከአቂላ ጋር በኤፌሶን ቤተክርስቲያን ታስተምር ነበር፤ ጳውሎስም ይህን ደብዳቤ የላከው ወደዚያችው ቤተክርስቲያን ነበር።

## “ወይም በወንድ ላይ ሥልጣን እንዲኖራት አልፈቅድም”

ርብቃ ሜሪል ግሮቱይስ እንዲህ ብለዋል፦ “በቁጥር 12 ላይ ያለው ጥቅስ ላይ ‘*ሥ*ልጣን’ የተባለው ቃል በሌላ በአዲስ ኪዳን ውስጥ አዎንታዊ ወይም ሕጋዊ የሆነውን *ሥ*ልጣንን ለማሳየት በጥቅም ላይ የዋለ ቃል አይደለም። ይህ ቃል በአዲስ ኪዳን በየትኛውም *ሥ*ፍራ አልተጠቀሰም። ከዚህም በላይ በጥንቱ ግሪክ ቋንቋ በርካታ ትርጉሞች አሉት። ብዙዎቹ ከተራ *ሥ*ልጣን የበለጠ ጠንካራ መልዕክት አላቸው፣ ጥቃት ማድረስንም ያመለክታል” (11)።

ጳውሎስ ጠባ-ጫሪነት፣ የበላይነት አመለካከት ማሳየትን ከለከለ፤ ይህ ደግሞ ለማንኛውም አማኝ ተገቢ *ሥ*ነምግባር አይደለም።

## “ዝም ትበል”

ሴቶች በጸጥታ መማር አለባቸው እንጂ ከአንድ ተማሪ የሚጠበቀውን *ሥ*ርዓት መጣስ የለባቸውም።

## “አዳም ቀድሞ ተፈጥሮአል”

በዘፍጥረት ውስጥ እግዚአብሔር “ከእውቀት ዛፍ” እንዳይበሉ ትዕዛዝ በቀጥታ ለአዳም ሰጥቶ ነበር። ይህ ሔዋን ሳትፈጠር የተሰጠ ነበር። ስለዚህ ሔዋን ከአዳም ቀጥተኛ ትዕዛዝ አልተቀበለችም። ርብቃ ሜሪል ግሮቱይስ ይህ በስፋት ሲያብራሩ “መታለልንና አደገኛ ስህተትን ለማስወገድ የእግዚአብሔር ቃል ዕውቀት በሙላት የሌላቸው (እንደ ሔዋንና የኤፌሶን ሴቶች ዐይነት) የእግዚአብሔር ቃል ዕውቀት ላላቸው ሰዎች (እንደ አዳምና በኤፌሶን ቤተክርስቲያን ውስጥ የነበሩ ወንድ መሪዎች) መገዛት አለባቸው ማለት ነው” (12)።

## “ልጅ በመውለድ ትድናለች”

ይህን ክፍል መረዳት አስቸጋሪ ነው፣ ነገር ግን አንድ ገለጻን እንመልከት፡ በኤፌሶን ውስጥ የነበረች አርጤምስ የምትባል ቤተመቅደስ በጥንቱ ዓለም አስደናቂ ከሚባሉ ሰባት ነገሮች መካከል አንዷ ነበረች። ትልቅና የግምጃ ቤት እንዲሁም 400 የጥበቃ ሠራተኞች ነበሩት። አርጤምስ ሴቶችን በወሊድ የምትረዳ ጣዖት ነበረች። ጳውሎስ ሴቶች በደህና ሁኔታ ልጆችን ለመውለድ ወደ አርጤምስ መመልከት የለባቸው፤ ከዚህ ይልቅ በኢየሱስ በማመን ደህና መሆን እንደሚችሉ ይነግራቸዋል። ሚሚ ሐዳድ እንዲህ ብለው ጽፈዋል፡ “በኤፌሶን የነበረውን የሐሰት ትምህርት ለመዋጋት፣ ጳውሎስ ሴቶች ልጅ በመውለድ እንደሚድኑ ተናገረ፡ ፡ ጳውሎስ ሴቶች ልጅ በመውለድ የሚድኑት አርጤምስን በማምለክ ሳይሆን በክርስቶስ በእምነት በመጽናት እንደሆነ ነውን?” (13)።

ክራግ ኬነር ወሳኝ የሆነውን ነጥብ ተናግረዋል፡ “መጽሐፍ ቅዱስ በጤናማ ሁኔታ ውስጥ የሴቶችን አገልግሎት ይፈቅዳል፣ ነገር ግን በአንዳንድ ልዩ ሁኔታዎች ውስጥ ግን ይከለክላል። ... ሴቶች መጽሐፍ ቅዱስን እንዳያስተምሩ የሚናገር አንዱ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ሴቶች የእግዚአብሔርን መልዕክት እንድናገሩ ከሚያበረታቱ በርካታ ክፍሎች ጋር ይቃረናል። ሴቶች እንዳያስተምሩ የታዘዙት በአንድ በተወሰነ ሁኔታ ውስጥ ነበር፤ ይኸውም ሐሰተኛ አስተማሪዎች ትኩረታቸውን በሴቶች ላይ ባደረጉበት አካባቢ ነው” (14)።

በማጠቃለያም በአንዳንድ በተወሰኑ ሁኔታዎች ውስጥ ካልሆነ በስተቀር አጠቃላይ የቅዱሳት መጻሕፍት ትምህርት ሁሉም የፀጋ ስጦታዎች ለወንዶችና ለሴቶች ተሰጥተዋል፤ ስለዚህ ሁሉም በሁሉም የአገልግሎት ደረጃዎች መሳተፍ እንዲችሉ ማበረታታት ነው። ግማሾቹ በሰንሰለት ታስረው በዓለም ውስጥ የእግዚአብሔር እጆችና እግሮች መሆን አንችልም!

# ራስነት

> ነገር ግን ይህን እንድታውቁ እወዳለሁ፣ የወንድ ሁሉ ራስ ክርስቶስ ነው፤ የሴትም ራስ ወንድ ነው፤ የክርስቶስም ራስ እግዚአብሔር ነው (1 ቆሮንቶስ 11:3)።

"ራስ" ወይም፲ "ከፓሌ" ብዙ ጊዜ ሥልጣን ተብሎ ይታሰባል። ነገር ግን "ምንጭም" ተብሎ ሊተረጎም ይችላል፤ ለምሳሌ እንደ ወንዝ መነሻ ሥፍራ ማለት ነው።

በ(1ቆሮንቶስ11፡3) ላይ ያለው "ራስ" የሚለው ቃል "ሥልጣን ያለው መሪ" ከመሆን ይልቅ "ምንጭ" ሊሆን የሚችልበት ሁለት ምክንያቶች ይኖራሉ። የመጀመሪያው የተዘረዘሩት ነገሮች የተጠቀሱት የግንኙነት ቅደም ተከተላቸውን (ከጊዜ አንፃር ቀዳሚና ተከታይነትን በሚያሳይ መልኩ ነው) ጠብቀው ነው። ግልበርት ብለዚክይን እንዲህ ብለዋል፡ "የእነዚህ ሦስት ሐረጎች ቅደም ተከተል የበላይና የበታች ሳይሆን ከጊዜ አንፃር ቀዳሚና ተከታይን በሚያሳይ ሁኔታ ነው፡ ፡ በፍጥረት፣ ክርስቶስ ለወንዶች የሕይወት ምንጭ ነበር ምክንያቱም ለአዳም ሕይወትን የሰጠው እርሱ ነበር። ከዚያ ደግሞ ወንድ ለሴት ሕይወትን ሰጠ፣ ምክንያቱም ሔዋን ከአዳም አጥንት ተገኘች። ከዚያም እግዚአብሔር ልጁ ሰው ሆኖ ወደ ዓለም ሲመጣ ሕይወትን ሰጠው። ሰዎች በእነዚህ ሐረጎች ቅደም ተከተል ውስጥ ጣልቃ ካልገባ፣ በዚህ ጥቅስ ውስጥ ያለው "ራስ" የሚለው ቃል ትርጉሙ ሕይወት ሰጪ ማለት ይሆናል"(15)።

ይህን ትርጉም በሕይታችን ማዛመዱ አስደናቂ ነው። ሚሚ ሐዳድ እንዲህ ብለው ጽፈዋል፡ "በዘፍጥረት እግዚአብሔር ሴትን ከወንድ አበጃት። በተመሳሳይ ሁኔታ ክርስቶስም የቤተክርስቲያን መሥራች ወይም ምንጭ ነው። ክርስቶስ በመሞት ለሰዎች ሕይወትን ሰጠ። በተመሳሳይ መንገድ ባሎች ሚስቶቻቸውን መስዋዕትነት በሚያስከፍል ፍቅር - እንደ ራሳቸው መውደድ አለባቸው። ይህ የአንድነት፣ የጥብቅ ወዳጅነት ማሳያ ነው" (16)።

## ጥያቄ

መጽሐፍ ቅዱስ ባል የቤተሰብ ራስ እንደሆነ በግልጽ ይናገራል አይደለም?

## መልስ

መጽሐፍ ቅዱስ ባል የቤተሰብ ራስ እንደሆነ አይናገርም፡ ፡ መጽሐፍ ቅዱስ የሚናገረው ወንድ የሴት ራስ እንደሆነ ነው፤ እግዚአብሔርም የክርስቶስ ራስ ነው፡ ፡ በዚህ ዐውድ ውስጥ "ራስ" የሚለው በሰዎች መካከልና በሥላሴዎች ውስጥ "የሕይወት ምንጭ" ነው ማለት ነው።

ሁለተኛ "ራስ" የሚለው "ሥልጣን ያለው መሪ" እንደሆነ መተርጎም በሥላሴዎች መካከል አንዱ ለሌላው መገዛት እንዳለ ያሳያል። ይህ ደግሞ በቤተክርስቲያን ታሪክ ውስጥ ትክክለኛ ያልሆነ ሐሰተኛ ትምህርት እንደሆነ ይታወቃል።

በዚህ ጥቅስ ውስጥ ያለውን "ከፓሌ" የሚለውን "ባለሥልጣን መሪ" በሚለው ሐሳብ ተርጉመን በጥልቀት እንመልከት፡

- ክርስቶስ የእያንዳንዱ ወንድ ባለሥልጣን መሪ ነው (አዎን)
- ወንድ በሴት ላይ ባለሥልጣን መሪ ነው (ምናልባት)
- እግዚአብሔር በክርስቶስ ላይ ባለሥልጣን መሪ ነው (ኢየሱስ ለዘላለም ለአባቱ የተገዛ አይደለም)

ከቪን ጊለስ እንዲህ ብለው ገልጸዋል፡ "ሁሉም ክርስቲያኖች ወልድ በምድር ላይ ሰው ሆኖ በነበረበት ወቅት ለአባቱ የተገዛ እንደነበር ይስማማሉ። የባሪያን መልክ በመያዝ አገልጋይ ነበር። ነገር ግን ብዙ ክርስቲያኖች የወልድ በምድር ላይ በነበረበት ጊዜ ለአባቱ መገዛት በዘላለም ወይም በሥላሴ ውስጥ ያለውን ቋሚ የአብና የወልድን ግንኙነት እንደሚገልጽ አያምኑም። በፊልጵስዩስ 2:5-11 ውስጥ ጳውሎስ ወልድ ራሱን ባዶ አድርጎ ሰው ሆኖ በመምጣት መስቀል ላይ ከመሞቱ በፊት ከአብ ጋር እኩል እንደነበር እንዲሁም ከሞት ከተነሣ በኋላ ደግሞ ጌታ ሆኖ እንደተሾመ ይናገራል" (17)።

ጥቅሱ የተሻለ ትርጉም የሚኖረው "ከፓሌ" "የሕይወት ምንጭ" ተብሎ ሲተረጎም ነው፡

- የወንድ ሁሉ ምንጭ ክርስቶስ ነው (አዎን)
- የሴት ምንጭ ወንድ ነው (አዎን- በፍጥረት ሴት ከወንድ ተገኘች)
- የክርስቶስ ምንጭ እግዚአብሔር ነው (አዎን- ሰው ሆኖ መወለድ ሂደት ኢየሱስ ከእግዚአብሔር ተላከ)

በመቀጠልም ኢየሱስ የቤተክርስቲያን ራስ እንደሆነ የሚገልጹ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን እንመልከት። እነዚህ ጥቅሶች የክርስቶስን ሚና እንደ መሪ ወይም ባለሥልጣን አይገልጹም። "ራስ" ኢየሱስ በዋናነት የሕይወት ምንጭና የድነት ምንጭና እንዲሁም የሚያሳድግ መሆኑን ይናገራሉ።

> እግዚአብሔር ሁሉን ከእግሩ በታች አስገዛለት፣ በቤተክርስቲያንም፣ በማንኛውም ነገር ላይ ራስ አድርጎ ሾመው። እርሷም ሁሉን ነገር በሁሉም ረገድ የሚሞላው፣ የእርሱ ሙላት የሆነች አካሉ ናት (ኤፌሶን1:22-23)።

ይልቁንም እውነትን በፍቅር እየተናገርን፣ ራስ ወደ ሆነው ወደ እርሱ በነገር ሁሉ እናድጋለን፤ እርሱም ክርስቶስ ነው። ከእርሱም የተነሣ አካል ሁሉ በሚያገናኘው ጅማት እየተያያዘና እየተጋጠመ፣ እያንዳንዱ ክፍል የራሱን ሥራ እያከናወነ በፍቅር ያድጋል፣ ራሱንም ያንጻል (ኤፌሶን 4:15-16)።

ይህ ሰው፣ አካል ሁሉ በጅማትና በማሰሪያ እየተጋጠመ ምግብንም እየተቀበለ እግዚአብሔር በሚሰጠው ማደግ ከሚያድግበት ራስ ከሆነው ጋር ግንኙነት የለውም (ቆላስይስ 2:19)።

ብለዚክይን እንዲህ ብለው ገልጸዋል፡ "አዲስ ኪዳን ስለተለያዩ መሪዎች የሚናገር በርካታ ክፍሎች አሉት፡ የሃይማኖ መሪዎች፣ የማሕበረሰብ መሪዎች፣ የጦር መሪዎች፣ የመንግሥት መሪዎች፣ የባሕል መሪዎች እና የቤተክርስቲያን መሪዎች ይናገራል፡ ፡ ከእነዚህ መካከል 'ራስ' ተብለው የተጠሩ ሰዎች አልነበሩም። ይህ ማለት በአዲስ ኪዳን ውስጥ 'ራስ' የሚለው ቃል ትርጉሙ 'መሪ' ማለት እንዳልሆነ ነው። ይህ 'ራስ' የሚለው ቃል በቆሮንቶስ፣ በኤፌሶንና በቆላሳይስ ውስጥ  በሥራ ላይ የዋለበት ሁኔታ ራስነት በአዲስ ኪዳን ውስጥ ክርስቶስ የሕይወትና የዕድገት ምንጭ እንዲሁም እንደ አገልጋይ ደግሞ ሕይወትን የሚሰጥና የሚያኖር መሆኑን የሚያሳይ መልዕክት እንዳለው እንድንደመድም ያደርገናል" (18)።

አሁንም ካላመናችሁ፣ የበርክሌይና የአልብራ ሚክልሴንን ጽሑፍ እንድታነቡ አደፋፍራችኋለሁ፡ "በአዲስ ኪዳን ከፓሌ ምን ማለት ነው?" አንዱ ሐሳብ እንዲህ ነው፡ "የግሪክ-እንግሊዘኛ ትርጉም መጽሐፍ ከጥንት ጀምሮ እስከ ዘመናዊው ግሪክ ድረስ ያለው ሁለት ክፍል ያለው ሲሆን ወደ 2000 ገጾች ያሉት በልዴል፣ ስኮት፣ ጆንስና ማክኬንዚ የተጻፈና የመጀመሪያው እትሙ በ1843 እአአ ታተመ…ይህ መዝገበ ቃላት ከፓሌ ምን ማለት እንደሆነ በተለያዩ ምሳሌዎች ይገልጻል። እነዚህ ዝርዝር ትርጉሞች ውስጥ "ሥልጣን"፣ የበላይ አለቃ"፣ "መሪ"፣ "ዳይሬክተር" ወይም ከዚህ ጋር የሚመሳሰል ትርጉም ያለው ነገር የለም" (19)። ሚክልሴንን በቀጣይነት ለአሥራ አራት ገጾች ስለ ግሪክ ይናገራሉ። ፊልጵ ባርቶን ፓይን ለሚክልሴንን በጻፉት የምላሽ ጽሑፋቸው ውስጥ እንዲህ ብለዋል፡ "ሚክልሴንስ በእርግጥ ላቀረቡት ጉዳይ የግሪክ አጠቃቀማቸው ደካማ/አነስተኛ ነው። በ1968 የታከለውን ሐሳብ ጨምሮ የልዴልና ስኮት የቃላት ፍቺ ውስጥ ከፓሌ በምሳሌያዊ አነጋገር ያለውን ትርጉም የሚገልጹ አርባ ስምንት የእንግሊዘኛ ቃላትን አውጥተው ነበር። ከእነዚህ ውስጥ አንዳቸውም ስለ መሪ፣ ሥልጣን፣ የመጀመሪያ ወይም የበላይ የሚል ትርጉም የላቸውም" (20)።

በማጠቃለያም ከሰው ልጅ ውድቀት የተነሣ ወንዶች ለአሳዛኝ የውድቀት ውጤት ተጋላጭ ቢሆኑም - ሚስቶቻቸው ላይ መግዛት- የእግዚአብሔር ሐሳብ ባሎች ለሚስቶቻቸው የሕይወትና የማበረታቻ ምንጭ እንደሆኑ ነው! ኢየሱስ ለእኛ እንደሆነ ማለት ነው!

ሜሪል ግሮቱይስ እንዲህ በማለት ያብራራሉ፥ "የሚስት ራስ የሚለውን ሐሳብ የሚስት መሪ በሚለው መንፈስ መረዳት መጽሐፍ ቅዱስ ራስ የሚለውን የሚስትን ሕይወት፣ ጤና እና ዕድገትን መንከባከብ የሚለውን ሐሳብ ማውደም ነው። ሴት ለራሷ ሕይወት ኀላፊነት መውሰድ የምትችልበት ዕድል ካልተሰጣት እንዲሁም እንደ ልጅ በሌላ ሰው የሚወሰንላት ከሆነ፤ በመንፈሳዊ፣ በስሜትና በአእምሮ ብስለት ወደ ሙሉ ሰውነት ማደግ የምትችልበት መንገድ የለም። ... የበላይና የበታች ያለበት ጋብቻዎችም የሁለቱ እኩል የሆኑ አጋሮች አገልግሎት በሚፈለግበት የክርስቶስ መንግሥት ውስጥ ባሎች በባሕርይ፣ በቅድስ፣ በማመርና በፍቅር ማደግ አይችሉም" (21)።

# መገዛት

> “ለክርስቶስ ካላችሁ አክብሮታዊ ፍርሀት የተነሣ አንዳችሁ ለአንዳችሁ ተገዙ። ሚስቶች ሆይ፣ ለጌታ እንደምትገዙ ለባሎቻችሁም ተገዙ ክርስቶስ፣ አካሉ ለሆነችውና አዳኟ ለሆናት ቤተክርስቲያን ራስ እንደሆነ ሁሉ፣ ባልም የሚስቱ ራስ ነውና። ባሎች ሆይ፣ ክርስቶስ ቤተክርስቲያንን እንደ ወደዳትና ራሱንም ስለ እርሷ አሳልፎ እንደ ሰጠ፣ እናንተም ሚስቶቻችሁን ውደዱ … ባሪያዎች ሆይ፤ ለክርስቶስ እንደምትታዘዙ፣ በምድር ጌቶቻችሁ ለሆኑት በአክብሮትና በፍርሀት፣ በልብ ቅንነትም ታዘዙ…። እናንተም ጌቶች ሆይ፤ ለባሮቻችሁ እንዲሁ አድርጉላቸው፤ የእናንተም ጌታ የሆነው በሰማይ እንዳለ፣ የሰውንም ፊት አይቶ እንደማያደላ ታውቃላችሁና አታስፈራሯቸው” (ኤፌሶን 5:21-22፣ 25፤ 6:5፣9)።

አንዱ ለሌላው መገዛት በዚህ ጥቅስ ውስጥ ቁልፍ መልዕክት ሲሆን በቤታችን ውስጥ በመንፈስ የተሞላ ሕይወት (ኤፌሶን 5፡18) ምን እንደሚመስል ያስተምራል። ጳውሎስ በዚያ ባሕል ውስጥ የነበረውን የሚስቶች ለባሎቻቸው መገዛትን እያንዳንዳችን ለአንዱ ለሌላው እንዴት እንደሚገዛ ምሳሌ አድርጎ ተጠቀመበት። ሚስቶችና ባሪያዎች መታዘዛቸው በአይሁድና በሮማውያን ሕግ ተቀባይነት የነበረው ባሕላዊ ልማድ ነበር። ነገር ግን ለመጀመሪያዋ ቤተክርስቲያን ቅድሚ የተሰጠው ወንጌልን መስበክ ነበር፤ ይህ ደግሞ በወቅቱ የነበረውን ሕግ የሚጣረስ ተግባር ነበር። ስለዚህ ጳውሎስ የወንድ የበላይነት በሚታይበት ኅብረተሰብ ውስጥ በመልካም የክርስቲያን ሥነምግባር - በመገዛት (መታዘዝ አይደለም) እና በመውደድ (ሕግ አይደለም) ነው።

ጂ. ሊ. ግራዲይ እንዲህ በማለት አጠቃልለዋል፡ “የክርስቶስን ፍቅር ለዓለም ለማሳየት መገዛት- የበላይ መሆን ወይም በሌላው ላይ መሰልጠን ሳይሆን አንዱ የራሱን መብት በመተው በክርስቶስ አካል ውስጥ የሚኖርበት ዘይቤ ነው” (22)።

## ጥያቄ

መጽሐፍ ቅዱስ ሚስቶች ለባሎቻቸው መገዛት እንዳለባቸው ያስተምራል፡ ፡ ይህ በእውቀትና በመደጋገፍ ላይ የተመሠረተ ሲሆን ነው አይደለም?

## መልስ

የሚስቶች መገዛትና የባሪያዎች መታዘዝ በአንደኛው መቶ ክፍለ ዘመን ይጠበቅ ነበር። ነገር ግን ለክርስቲያን ቤተሰቦች ጳውሎስ በአዲስ መንገድ አብረው እንዲኖሩ ያዛቸዋል፡ አንዱ ለሌላው መገዛትን!

# መደምደሚያ

በአብዛኛው ሴቶችና ወንዶች ከጤናማ ግንኙነትና ስኬታማ አገልግሎት የሚጎድሉበት አንዱ ምክንያት ጥቂት የቅዱሳት መጻሕፍትን ጥቅሶች የሚተረጉሙበት መንገድ ነው። ይህ የተከሰተው ለመጀመሪያ ጊዜ አይደለም፡፡ በዩናይትድ ስቴትስ በ1800ዎቹ የባሪያ ንግድን ይደግፉ የነበሩ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስን በሚመቻቸው መንገድ ተርጉመው ይጠቀሙበት ነበር። ኢየሱስ በምሳሌው ውስጥ ባሪያ የሚለውን ሐሳብ ተጠቅሟል፣ በገላትያ ምዕራፍ 4 ውስጥ ባርነትን እንደ መግለጫ ሲጠቀምበት እንዲሁም በኤፌሶን ምዕራፍ 6 ውስጥ ባሮች ለጌቶቻቸው መታዘዝ እንዳለባቸው መጠቀሱን እንደ ምክንያት ይናገራሉ። ስታን ጉንድራይ እንዲህ ብለዋል፡ "በአሥራ ዘጠነኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጽሐፍ ቅዱስን ለባሪያ ንግድ ድጋፍ እንደሚሰጥ ሲከራከሩ የነበሩ አሁን እንዳፈሩ ሁሉ፤ አንድ ቀን ክርስቲያኖች ቤተክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱስን የወንድ የበላይነትን ለመጠበቅ በመጠቀሟ ማፈራቸው አይቀርም" (23)።

ቅዱሳት መጻሕፍት እንደ ዐውዱ፣ ወቅቱና አጠቃላይ አብይ መልዕክቶች መተርጎም አለበት። ከዚህ በታች የተጠቀሱ ሁኔታዎች ከአጠቃላይ የመጽሐፍ ቅዱስ መልዕክት ጋር የሚጣጣሙ እንደሆኑ ተመልከቱ፡:

- በመንፈስ የተነቃቃች የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪ የሆነች አንዲት ሴት ለማዕበረ ምዕመናን አጭር ምስክርነት እንድትሰጥ ትጠየቃለች፣ ነገር ግን ምስክርነቷ እንደ ትምህርት እንዳይታይ በመድረኩ የተወሰነ ሥፍራ እንድትቆም ትጠየቃለች
- እናት ጥናት በማድረግ ያገኘችውን ሕክምና የእርሷ ልጅ እንዳያገኝ ይከለከላል ምክንያቱም ባሏ አልተስማም፣ እምቢ አለ።
- አገልግሎቷን እጅግ መልካም በሆነ መንገድ በማከናወን እያሳደገች ያለች አንዲት ሴት ጥቂት ወንዶች ወደ ቦርድ መጥተው ሴቶች በመሪነት ቦታ ላይ መሳተፍ የለባቸውም የሚል እምነት ስላላቸው ሴቲቱ ከአገልግሎት ተባረረች።

- ሚስት ቤተክርስቲያን ውስጥ ዲያቆን በሆነው ባሏ በቃልና በአካል ጥቃት ይደርስባታል። የእርሷ መጋቢ ባሏን ማስቆጣት እንደሌለባት ነገር ግን ለእርሱ መገዛትና መጸለይ እንዳለባት መከራት።
- በኮሌጅ ትምህርት በጣም መልካም እምርታ እያሳየች ያለች ሴት ትምህርቷን እንድትተው ተመከረች፤ ለእርሷ ፍጹም የሆነው የእግዚአብሔር ፈቃድ ወደፊት ማግባት ነው። የውጭ ሥራዎችን እየሠራች ባሏን በበቂ ሁኔታ ማገልገል እንደማትችል ተነገራት።

የሚገርመው ነገር በዚህ ርዕስ ጉዳይ ላይ የተለያዩ ሐሳቦች ይኖራሉ። ነገር ግን ብንሳሳትም፣ የእግዚአብሔርን ሥራ በሚያደናቅፍ መንገድ መሳሳት የለብንም፡፡ ሁሉም የክርስቶስ አካል ሁሉንም ጸጋውን ለዓለም ሁሉ መጠቀም እንዲችል እናበረታታ። ያሉ ፍላጎቶች ብዙ ናቸው፤ እግዚአብሔር ደግሞ ሁሉም ሰው እንደሚያስፈልግ ያውቃል!

# ስለ ክርስቲያኖች ለመጽሐፍ ቅዱስ እኩልነት (ሲቢኢ)

ክርስቲያኖች ለመጽሐፍ ቅዱስ እኩልነት (ሲቢኢ) ለጥቅም ያልተመሠረተ መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት ሆኖ መጽሐፍ ቅዱስ በትክክል ቢተረጎም በማንኛውም ጎሳ፣ የኢኮኖሚ ደረጃና የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ወንዶችና ሴቶች እኩል መሆናቸውን መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምራል ብለው የሚያምኑ ክርስቲያን ወንዶችና ሴቶች የተመሠረተና የሚደገፍ ድርጅት ነው። የድርጅቱ ሐሳብ የተመሠረተው በቅዱሳት መጻሕፍት ትምህርት ለምሳሌ ገላ3:28 ላይ ነው:

"በአይሁድና በግሪክ፣ በባሪያና በነጻ ሰው፣ በወንድና በሴት መካከል ልዩነት የለም፤ ሁላችሁም በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ናችሁ"

## ተልዕኮ

ክርስቲያኖች ለመጽሐፍ ቅዱስ እኩልነት የሚለው ድርጅት የሚኖረው መጽሐፍ ቅዱስ ሴቶችና ወንዶች እኩል አገልግሎትና መሪነትን በቤተሰብ፣ በቤተክርስቲያንና በዓለም ውስጥ መጋራት እንዳለባቸው በማስተማር መጽሐፍ ቅዱሳዊ ፍትህንና ማሕበረሰብ እንዲኖር ማበረታታት ነው።

## መሠረታዊ እሴቶች

1. መጽሐፍ ቅዱስ ለእምነት፣ ሕይወትና ተግባራችን የበላይ መመሪያችን ነው።
2. የወንድ የበላይነት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሞዴል ሳይሆን የኀጢአት ውጤት ነው።
3. የወንድ የበላይነት ሥልጣንን ያለአግባብ መጠቀም ነው፤ እግዚአብሔር ለሴቶች የሰጣቸውን ነገሮች፡ ክብራቸውን፣ ነጻነታቸውን፣ መሪነታቸውና ብዙውን ጊዜ ሕይወታቸውን ከእነርሱ መውሰድ ነው።
4. መጽሐፍ ቅዱስ የወንድ የበላይነት ባሕልን ቢያንጸባርቅም፣ መጽሐፍ ቅዱስ በሰብዓዊ ግንኙነት ውስጥ የወንድ የበላይነትን አያስተምርም።

5. የክርስቶስ የቤዛነት ሥራ ሁሉንም ሰዎች ከወንድ የበላይነት እርነት ያወጣቸዋል፤ ሴቶችና ወንዶች በአገልግሎትና በመሪነት እኩል ሥልጣን እንዲጋሩ ይጋብዛቸዋል።
6. የእግዚአብሔር ዕቅድ ለግንኙነቶች በወንድና ሴት መካከል በታማኝነት ላይ የተመሠረተ ጋብቻ፣ መልካም የሆነ ላጤነት እና በክርስቲያን ማሕበረሰብ ውስጥ አንዱ ለሌላው መገዛትን ያጠቃልላል።
7. ያልተገደበ የሴቶችን ስጦታዎች መጠቀም የመንፈስ ቅዱስ አንዱ ሥራ ነው ሲሆን ወንጌልን ለዓለም ለማዳረስ ወሳኝ ሚናን ይጫወታል።
8. የክርስቶስ ተከታዮች ኢፍትሐዊነትንና የወንድ የበላይነት ትምህርቶችንና ሴቶችንና ወንዶችን የሚያገልና ለጥቃት የሚያጋልጠውን ተግባራትን መቃወም አለባቸው፥

## ራእይ

ክርስቲያኖች ለመጽሐፍ ቅዱሳዊ እኩልነት ራእይ አማኞች ሁሉ በክርስቲያን ማሕበረሰቦች ሙሉ ድጋፍ ስጦታዎቻቸውን በነጻነት ለእግዚአብሔር ክብርና ዓላማ የሚጠቀሙበትን ዐውድ ማየት ነው።

# ዋቢ መጻሕፍት

(1) Linda Belleville, *Two Views on Women in Ministry* (Zondervan Publishing House, 2001; Grand Rapids, MI; James Beck and Craig Blomberg, eds.). 142.

(2) Ibid., 148.

(3) Rebecca Merrill Groothuis, *Good News for Women* (Baker Book House, 1997; Grand Rapids, MI). 43.

(4) Gilbert Bilezikian, *Beyond Sex Roles* (Baker Academic, 2006; Grand Rapids, MI). 99-100.

(5) John Phelan, *All God's People* (Covenant Publications, 2005; Chicago, IL). 51.

(6) Mimi Haddad, "What Language Shall We Use?" (*Priscilla Papers*, Volume 17, Issue 1, Christians for Biblical Equality; Minneapolis, MN).

(7) Richard and Catherine Kroeger, "Why Were There No Women Apostles?" (*Equity*, 1982). 10-12.

(8) David Claydon, "The Context for the Production of the Lausanne Occasional Papers," (*Empowering Women and Men to Use their Gifts Together in Advancing the Gospel*, *Lausanne Occasional Paper No.* 53; Christians for Biblical Equality, 2005; Minneapolis, MN; Alvera Mickelsen, ed.). iv.

(9) Bilezikian, *Beyond Sex Roles*, 140.

(10) Craig Keener, *Two Views on Women in Ministry* (Zondervan Publishing House, 2001; Grand Rapids, MI; James Beck and Craig Blomberg, eds.). 166, 169, 171.

(11) Groothuis, *Good News for Women*, 215.

(12) Ibid., 222.

(13) Mimi Haddad, "Paul and Women," (*Empowering Women and Men to Use their Gifts Together in Advancing the Gospel*, *Lausanne Occasional Paper No.* 53; Christians for Biblical Equality, 2005; Minneapolis, MN; Alvera Mickelsen, ed.). 34.

(14) Keener, *Two Views on Women in Ministry*, 29.

(15) Gilbert Bilezikian, "I Believe in Male Headship" (Christians for Biblical Equality, Free Articles, cbeinternational.org; Minneapolis, MN).

(16) Haddad, "Paul and Women," 35.

(17) Kevin Giles, "The Subordination of Christ and the Subordination of Women," (*Discovering Biblical Equality*; InterVarsity Press, 2004; Downers Grove, IL; Ronald Pierce and Rebecca Merrill Groothuis, eds.). 337.

(18) Bilezikian, *Beyond Sex Roles*, 122.

(19) Berkeley and Alvera Mickelsen, "What Does Kephale Mean in the New Testament?" (*Women*, *Authority & the Bible;* InterVarsity Press, 1986; Downers Grove, IL; Alvera Mickelsen, ed.). 97-98.

(20) Phillip Barton Payne, "Response," (*Women*, *Authority & the Bible;* InterVarsity Press, 1986; Downers Grove, IL; Alvera Mickelsen, ed.). 118.

(21) Groothuis, *Good News for Women*, 157-158.

(22) J. Lee Grady, *Ten Lies the Church Tells Women* (Charisma House, 2000; Lake Mary, FL). 177.

(23) Stan Gundry, "From *Bobbed Hair*, *Bossy Wives*, *and Women Preachers* to *Woman Be Free*: My Story" (*Priscilla Papers*, Volume 19, Issue 2, Christians for Biblical Equality; Minneapolis, MN).

“ጎን ለጎን የሚለው መጽሐፍ በጥልቀት መጽሐፍ ቅዱስን ካለማንበብ ለሚመጣው ግራ መጋባትና የቤተክርስቲያንን አገልግሎትና በዓለም የምታደርገውን ምስክርነት የሚያዳክመውን የሥርዓተ ጾታ አድልዎን ለመቅረፍ ኃይለኛና ምጥን መፍትሔ ናት። በግልና በቡድን ለማጥናት ጥሩ መጽሐፍ ነች። ጎን ለጎን በሥርዓተ ጾታ ላይ ያሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ በርካታ አብያተ ክርስቲያናት ሊጠቀሙበት የሚገባ ትልቅ ሀብት አጭር ናት።”

**ሚሚ ሐዳድ**

የክርስቲያኖች ለመጽሐፍ ቅዱስ እኩልነት ፕረዜዳንት

www.cbeinternational.org

“ጎን ለጎን የሚለው መጽሐፍ ስለመጽሐፍ ቅዱሳዊ እኩልነት አጭርና ግልጽ በሆነ መንገድ ማብራሪያ የሚሰጥ መጽሐፍ ነው”

**አልቬራ ሚክልሴን**

የክርስቲያኖች ለመጽሐፍ ቅዱሳዊ እኩልነት መሥራች አባል፣ ደራሲ፣ አርታኢና መምህር

ጃኔት ጆርጅ በክርስቲያኖች ለመጽሐፍ ቅዱስ እኩልነት ድርጅት ውስጥ በዳይሬክተሮች ቦርድ አባልነት አገልግለዋል። በአሁኑ ጊዜ በኢንላይተን ፋውንዴሽን ውስጥ መንፈሳዊ ዳይሬክተር በመሆን እያገለገሉ ይገኛሉ። ጃኔትና ባለቤታቸው ማት በሴንተኒል ኮሎራዶ የቤት ግምትና ሽያጭ ላይ የሚሠራ የንግድ ድርጅት ያላቸው ሲሆን በዚያው ከተማ የኦሲስ ቤተክርስቲያን አባል ናቸው። ሁለቱም ሶስት ያደጉ ሴት ልጆች አሉአቸው።

ከበደ በከሬ የሥነልቦና ባለሙያና ደራሲ ሲሆኑ ከዚህ በፊት 12 መጻሕፍትን በአማርኛ ለሕትመት አበቅተዋል። አቶ ከበደ በርካታ ጽሑፎችን፣ የሥልጠና ማኑዋሎችንና መጻሕፍትን ከእንግሊዘኛ ወደ አማርኛና ኦሮምኛ ቋንቋዎች ተርጉመዋል። በአሁኑ ጊዜ ከመጻፍና ከማስተማር በተጨማሪ በሥነልቦና እና በማሕበራዊ ጉዳዮች ላይ በአማካሪነት እየሠሩ ይገኛሉ። ከበደና ባለቤታቸው ወ/ሮ ዘወዲቱ በአዲስ አበባ ይኖራሉ፤ አንዲት ሴት ልጅና ሦስት ወንድ ልጆች አላቸው።

ጎን ለጎን፡ የመጽሐፍ ቅዱሳዊ እኩልነት አጭር ማብራሪያ የሚለውን መጽሐፍ ለማግኘት/ለማዘዝ የሚከተለውን አድራሻ መጠቀም ትችላላችሁ:
ድሕረ ገጽ: www.equalitydepot.com
ስልክ: 612-872-6898
ኢሜይል: books@cbeinternational.org

የሽፋን ሥዕል በሜሪ ክውንት

ISBN 978-1-939971-28-9
90000
9 781939 971289

CBE International

Christians for Biblical Equality
122 W Franklin Ave, Suite 218
Minneapolis, MN 55404-2451
Phone: 612-872-6898